# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 93 የካቲት 18 2002 ዓ.ም


ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ፣ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## መለስ ዜናዊ ተቃዋሚዎቹን እንክርዳዶች፣ ጭቃዎችና ገለባዎች ሲል መሳደቡ ተዘገበ

ህወሀት የተመሰረተበትን 35ኛ አመት በዓል ለማክበር ፋሽስቱና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በመቀሌ ከተማ ባደረገው ንግግር ተቃዋሚዎቹን በተለይም የቀድሞ የትግል አጋሮቹን "ጭቃ ፣ ገለባ፣ እንክርዳድ" በማለት የስድብ ውርጅብኝ ያወረደባቸው ሲሆን፣ አስተያየት ሰጪዎች ግን ግለሰቡ የገባበትን የዝቅጠት ደረጃ በስድብ ለመሸፋፈን እየሞከረ ነው ይላሉ።

አምባገነኑ መለስ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ተቃዋሚዎች ሲገልጽ "ጠላቶቻችን ስርአቱን በአይነ ቁራኛ የሚመለከቱ፣ እንደኮሶ መሯቸው መጨረሻ የሌለው ጥላሸት የሚቀቡ፣ ከትግራይ የተገኙ እንክርዳዶችን ተሸክመው በህዝባችን ዲሞክራሲ ፣ ሰላምና ልማት ቀዳዳ ለማግኘት የሚጥሩ ናቸው" ሲል ፈርጇአቸዋል።

በፍጹም ስሜት ውስጥ ሆኖ ይናገር የነበረው መለስ ዜናዊ ተቃዋሚዎቹንና በተለይም የቀድሞ የትግል አጋሮቹን ህዝቡን ወደ ሀይል እንዲያመራ ለማድረግና እነርሱ ጭቃ እንደሆኑት ሁሉ ህዝቡንም ጭቃ ሊያደርጉት እየተንቀሳቀሱ ነው ሲል ክስ አቅርቧል።

መለስ ዜናዊ በተለመደ የትእቢት ንግግሩ "የምንገነባው ስርዓት የእኛ እርጋፊ የሆኑ ወገኖችንም እንዲያስተናግድ ተደርጎ የተሰራ ነው" ያለ ሲሆን፣ "የካቲት 11ም ለትግራይ ህዝብ ዳግም የልደት በአል ነው" ሲል ተናግሯል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የመከላከያ ሰራዊት አባላት መሳሪያቸውን እንዲያስረክቡ እየተደረገ ነው

ስማቸው እንዳይገለጽ ያስጠነቀቁ አንድ የመከላከያ ሰራዊት አባል ለሪፖርተራችን እንደገለጸው ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በባህር ዳር ከተማ በተለምዶ መኮድ እየተባለ በሚጠራው ወታደራዊ ክፍል ውስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙ ወታደሮች በተሰጣቸው አስቸኳይ ትእዛዝ መሰረት የጦር መሳሪያቸውን እያስረከቡ ነው። ዘጋቢያችን እንደገለጸልን ወታደሮቹ ለረጂም ጊዚያት ይዘውት የነበረውን የጦር መሳሪያ በአሁኑ ሰዓት እንዲመልሱ አስቸኳይ ትእዛዝ የመጣበት ምክኒያት ምናልባት ከምርጫው ጋር በተያያዘ በሃገሪቱ በተለይም በአማራው ክልል ሊፈጠር ይችላል ተብሎ የሚገመተዉን አለመረጋጋትና ግርግር በቀላሉ ለመቆጣጠር እችላለሁ ከሚል ከንቱ ቅዠት እንደሆነ ገልጸዋል። እጅግ በጣም የሚያሳዝነው ግን መሳሪያዎቻቸውን እንዲመልሱ የሚደረጉት ከትግራይ ተወላጆች ውጭ ያሉ የሌሎች ብሄር አባላት ሲሆኑ፣ ለአገዛዙ ታማኝ የሆኑ የህወሀት አባላት መሳሪያዎቻቸውን እንደያዙ ይቆያሉ።

ከዚሁ ዜና ጋር በተያያዘ ዘጋቢያችን ለአስተያየት ሰጪው የሰራዊቱ አባል 'ወያኔ በዚህ መልክ የጦር ሰራዊቱን መጫወቻ ለማድረግ መሞከሩን እንዴት ትመለከተዋለህ?' በማለት ላቀረበለት ጥያቄ በሰጠው ምላሽ "በርግጥ ወያኔ በአንዳንድ ለጥቅማቸው ባደሩ ሆዳም የሰራዊቱ ባለማእረግና ተራ ወታደሮች አማካኝነት የመከፋፈልና እርስ በርስም ጥርጣሬ እንዲኖር ሌት ከቀን እየሰራ ቢሆንም፣ በጦሩ ውስጥ ያሉት እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ግን አመቺ የሆነ ጊዜና ሁኔታን አድፍጠው እየተጠባበቁ እንደሆነ በመግለጽ ያቺ አመቺ የሆነች ሁኔታና ጊዜ ስትደርስ ግን ለወያኔ ይብላኝለት" በማለት አስተያየቱን አጠናቋል።

በሌላ በኩል አሁን ወያኔ በከተሞች ውስጥ የሚገኙ የሌሎች ብሄር ተወላጆችን ትጥቅ ማስፈታቱ በምርጫ 97 ዓ.ም ከወሰደው እርምጃ ጋር እንደሚመሳሰል ታውቋል። በምርጫ 97 ወቅት ከትግራይ ብሄር ውጭ ያሉ የአዲስ አበባ ፖሊስ አባላት መሳሪያዎቻቸውን እንዲያስረክቡ መደረጋቸው የሚታወስ ሲሆን፣ በአሁኑ ሁኔታ ግን ከፖሊስ ሰራዊት አባላት በተጨማሪ የመከላከያ አባላትም ትጥቅ እንዲፈቱ እየተደረገ ነው። ይህም ወያኔ እየወሰደ ያለው እርምጃ አገዛዙ ምን ያክል በአለመረጋጋት ችግር ውስጥ እንዳለ የሚያሳይ ነው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ኤርትራዊያን በአገራቸው ላይ የተደረገውን ማእቀብ ተቃወሙ

በተለያዩ የአውሮፓና የአሜሪካ ከተሞች የሚገኙ ኤርትራዊያን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በአገራቸው ላይ የጣለውን ማእቀብ ባለፈው ሰኞ በነቂስ ወጥተው እንዳወገዙ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ዘገቡ። በአውስትራሊያ፣ በስዊዘርላንድና በአሜሪካ በተደረጉት ሰላማዊ ሰልፎች ቁጥሩ ከዚህ በፊት ታይቶ የማያውቅ እጂግ በርካታ ህዝብ መገኘቱንና ኢትዮጵያውያንም የሃገራቸውን ባንዲራ አንግበው በሰልፉ መሳታፋቸውን ከተገኘው ዜና ለመረዳት ተቺሏል። ታላቁና ታውቂው የብሪታኒያ የዜና ምንጪ ቢ.ቢ.ሲ. እንደዘገበው ሰልፈኞቹ በኤርትራ ላይ የተጣለውን ማዕቀብ በጽናት እንደሚቃወሙና ለመንግስታቸው ደማቸዉን ገንዘባቸዉንና ያላቸውን ማናቸውንም ነገር ለመስጠት ወደኋላ እንደማይሉ ገልጿል። በአውሮፓ ውስጥ በስዊትዘርላንድ የተባበሩት መንግስታት ጽ/ቤት ፊት ለፊት በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ከስዊድን፤ ከኖርዎይ፤ ከዴንማርክ፣ ከጀርመን፤ ከሆላንድ፤ ከእንግሊዝ፤ ከቤልጂየም፤ ከጣሊያንና ከሌሎች ያውሮፓ ሃገሮች የተውጣጡ ኤርትራዊያንና የአፍሪካ ቀንድ ተወላጆች እንደተሳተፉበት፤ የየሃገሩ ተወካዮችም ማዕቀቡን በመቃወም ንግግር እንዳደረጉ ከስፍራው የደረሰን ዜና ያረጋግጣል። በተመሳሳይ መልኩ በአሜሪካን ሃገር በስቴት ዲፓርትሜንት ፊት ለፊት በተደረገው ትእይንተ ህዝብ ከአስር ሺህ ሰው በላይ እንደተሳተፈበትና በሰልፉም ሽማግሌዎች፣ አዛውንቶች፤ ወጣቶችና ህጻናት ሳይቀሩ መሳተፋቸው ታውቋል። በሰልፉ ላይ ከተገኙት ኢትዮጵያዊያን መካከል እውቁ የሰብዓዊ መብት ታጋይ አክቲቪስትና ጸሃፊ አቶ ናእምን ዘለቀ በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ንግግር እንዳደረጉ ለግንቦት ሰባት ድምጽ በሰጡት አጭር ቃለመጠይቅ አስታውቀዋል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሚስጥራዊ ስብሰባ አደረገ

በአማራ ክልል በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በተለምዶ ፔዳጎጂ በሚባለው የዩኒቨርሲቲው ዋና ቅጥር ጊቢ በተለያዩ ጥቅሞችና ማስፈራሪያዎች አስገድዶ አባል ያደረጋቸው የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና ለጥቅማቸው ሲሉ ለአገዛዙ ያደሩ የዩኒቨርሲቲው ሆድ አደር ሰራተኞች ከክልሉ የወያኔ አገዛዝ ቅጥረኞች ጋር በመሆን ሚስጥራዊ ስብሰባ ያደረጉ መሆናቸውን ስማቸው እንዳይገለጽ በጥብቅ ያስጠነቀቁት በስብሰባው የተሳተፉ የዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎች በስልክ የገለጹለትን መሆኑን በመጥቀስ አዲስ አበባ የሚገኘው የግንቦት ሰባት ዘጋቢያችን ለዝግጂት ክፍላችን አስታውቋል።

ዘጋቢያችን መረጃዉን ጠቅሶ እንደገለጸው ስብሰባው የተካሄደው ማክሰኞ ጥር 15 ቀን 2002 ዓም መሆኑን ጠቅሶ ስብሰባው ያተኮረበትም ዋናው ርዕስ በመጪው የግንቦት ወር ሊካሄድ እየታሰበ ባለው የይስሙላ ምርጫ ዙሪያ መሆኑንና በዚህም ምርጫ ሂደት ወያኔ ከህብረተሰቡ ሊደርስብኝ ይቺላል ብሎ ያሰበውን ተቃውሞና ግርግር በመፍራት መሆኑን ተናግሯል። ዘጋቢያችን የወያኔው አገዛዝ የክልሉ ቅጥረኞች ከምርጫው ጋር በተያያዘ የምርጫው ሂደት ፍጹም ሊዋጥለት ያልቻለው ህብረተሰብ ውስጣዊ ቁጪቱ ድንገት ገንፍሎ እንዳይወጣ እነኚህን ያገዛዙ አባል የሆኑ ተማሪዎችን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የምትካሄደዋን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በሚስጥር በመከታተል ሪፖርት እንዲያቀርቡ ያስጠነቀቋቸው መሆኑን ጠቅሷል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔው አገዛዝ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በመላው ኢትዮጵያ አዳርሻለሁ ቢልም አለማቀፍ ድርጅቶች ግን አጣጥለውታል

ከትናንት በስቲያ በተባበሩት መንግስታት የስብሰባ ማዕከል በተከፈተውና በርካታ ተሳታፊዎች በተገኙበት የትምህርት ለሁሉም ከፍተኛ ቡድን ጉባኤ የወያኔው አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጣጠር በ 2015 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ለማዳረስ ተይዞ የነበረውን ግብ እውን እናደርጋለን በማለት የተለመደ ዲስኩሩን ማሰማቱን የተለያዩ የብዙሃን መገናኛ አውታሮች ገለጸዋል። በሌላም በኩል በዚሁ ስብሰባ ለመሳተፍ ከመጡት የተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ አንዱ የሆነው ግሎባል ካምፔይን ፎር እዱኬሽን የተባለው ዓለም አቀፍ የሲቪል ማህበረሰብ ባወጣው መግለጫ የመለስን ንግግር ተዓማኒነት የጎደለው መሆኑን በማረጋገጥ በአለም ዓቀፉ የኢኮኖሚ ቀውስ ምክኒያትለትምህርት የተያዘው ዓለም ዓቀፍ ግብ ፍጹም ተባራዊ ሊሆን እንደማይችል ያለውን ፍራቻ መግለጹ ታውቋል።

ተአማኒነት ያላቸውና የገንዘብ ልገሳውን የሚያደርጉት ሃገራት አካል የሆኑት እነኝህ ዓለም አቀፍ ተቋማት ከፍተኛ የሆነ ስጋታቸውን እየገለጹ ባሉበት ሁኔታ መለስ ዜናዊ ለጋሾች ቃል የገቡትን ርዳታ ባይሰጡንም (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ



## ዘረኝነትን መቃወም እና ወያኔን ለማስወገድ መጣር ለራሱ ክብር ከሚሰጥ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ የሚጠበቅ ተግባር ነው!!!

የግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የወያኔ ዓይነት ለከት የለሽ ዘረኝነት በሃገራችን ታሪክ ታይቶ የማይታውቅ እንደሆነ የሚያስረዱ ማስረጃዎችን ለሕዝብ እያቀረበ ነው፡፡

የእነዚህ ዘረኞች ዓላማ የኢትዮጵያን ሕዝብ እየረገጡ መግዛት ነው፡፡ ፍላጎታቸው እስከዛሬ ከታዩት ገዥዎች እጅግ የላቀ የቅንጦት ሕይወት በኢትዮጵያ ሕዝብ ኪሳራ መኖርና ይህንንም ለልጅ ልጆቻው ማስተላለፍ ነው።

የግንቦት 7 ንቅናቄ የወያኔን ዓይን ያወጣ ዘረኝነት ካሳየባቸው ማስረጃዎች አንዱ ከጥቂት ወራት በፊት ይፋ የሆነው በወያኔ ሠራዊት ውስጥ ያለውን የከፍተኛ መኮንኖች የብሄር/ብሄረሰብ ስብጥር የሚያሳየው ጥናት ውጤት ነው፡፡ ይህ ጥናት ወያኔ "የኢትዮጵያ መከላከያ" እያለ የሚጠራው የጦር ድርጅት ውስጥ ከ95 በመቶ በላይ የሚሆነው ከፍተኛ ሥልጣን የተያዘው የወያኔ አባላት በሆኑ የትግራይ ተወላጆች እንደሆነ ስም ዝርዝራቸውን በማውጣት አጋልጧል። ይህ ጥናት የብዙዎችን ዓይን ከፍቷል። የወያኔ ዓይን አውጣ ዘረኝነት ለሀገሩ የሚቆረቆርና ለራሱ ክብር ያለውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ አስቆጥቷል። ከኢትዮጵያዊያንም አልፎ ከራሳቸው ጠባብ ጥቅም እየተነሱ የወያኔን ወንጀሎች በቸልታ የሚመለከቱትን የውጭ መንግሥታትንም አስደንግጧል። የዘረኞች ቁንጮ የመለስ ዜናዊ ምላሽ ግን ስጋታቸውን የገለፁ የአሜሪካ ባለስልጣንን ‹‹ደደብ›› ብሎ መስደብ ሆነ፡፡

በግንቦት 7 የጥናትና ምርምር ቡድን ለወጣው ማስረጃ የመለስ ዜናዊ ምላሽ በስድብና ድንፋታ ብቻ ሲገለጽ ይህ ግለሰብ ባቋቋመው ዘረኛ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ተጠቃሚ የሆኑ ግለሰቦችና ቡድኖች ግን ከጌታቸው ድንፋታ አልፈው ዘረኛው ሥርዓት ትክክልም ተገቢም መሆኑን ለመግለጽ ሞክረዋል፡፡ አንዳንዶች የመለስን በትግራይ ጄነራሎች የተሞላ የወታደራዊ ሥልጣን ድልድል ትክክለኛት ለማስረዳት ከወያኔ በፊት የነበሩት የአጼ ኃይለስላሴንና የደርግ አገዛዝ ሥርዓቶች ተመሳሳይ በሆነ ዘረኛ መንገድ ሠራዊታቸውን አደራጅተው የነበሩና የወያኔ አገዛዝ ለምን ተለይቶ እንደሚኮነን እንደማይገባቸው ዓይን አውጥተው ለመከራከር ሲሞክሩ ተስተሏል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ የእነዚህ ዘረኞች ክርክር ምን ያህል ዓይን ያወጣ፣ የይሉኝታ ቢስ ዘረኞችና ሆድአደሮች ክርክር እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብና የዓለም ማኅበረሰብ እንዲረዳው በአጼ ኃይለስላሴና በደርግ የአገዛዝ ዘመን የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ከሜጀር ጀኔራልነት ማእረግ በላይ ሥልጣን የነበራቸውን መኮንኖች ብሄረሰባዊ ስብጥር የሚያሳይ ጥናት ባለፈው ሣምንት ይፋ አድርጓል፡፡ ይህ ጥናት እንዳረጋገጠው ወያኔ የአማራ ትምክህተኛና ነፍጠኛ እያለ ሲኮንናቸው በነበሩት አገዛዞች ውስጥ ዛሬ እሱ እየተገበረው ያለውን ዓይነት ዓይን ያወጣ ዘረኛ የሥልጣን ድልድል ማግኘት አይቻልም፡፡ ለዚያውም እነዚህ ሥርዓቶች ራሳቸውን የብሄረሰቦች እኩልነት መገለጫ አድርገው የሚቆጥሩ እንዳልነበሩ ልብ ይሏል።

ጥናቱ እንደሚያሳየው ከወያኔ በፊት በነበሩት ሁለት ሥርዓቶች ውስጥ የሃገሪቱ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች በቁጥርም ይሁን በስብጥር ከተለያዩ የሃገሪቱ ብሄረሰቦች የተውጣጡ ነበሩ፡፡ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ከሜጀር ጄኔራልነት በላይ የነበረው ሥልጣን 55 ከመቶው በአማራ ተወላጆች የተያዙ ቢሆንም በተለይ ወያኔዎች የፕሮፓጋንዳቸው ጥቃት አድርገውት ከኖሩት የሸዋ አማራ የመጡት 20 በመቶው ብቻ እንደነበሩ ጥናቱ ያሳያል፡፡ 15.5 ከመቶ የሚሆነው የጄነራልነት ማእረግ የተያዘው ከተለያዩ ብሄረሰቦች የተቀላቀሉ ተወላጆች ሲሆን ዛሬ የብሄረሰቦች እኩልነት ተረጋግጧል እያሉ ወያኔዎች በሚያናፉበት ዘመን አንድም ከፍተኛ ጄነራል በሠራዊት አዛዥነት ለመወከል ያልቻለው ታላቁ የኦሮሞ ብሄር በንጉሱ ዘመን እንኳን 13.3 በመቶ የጄነራልነቱን ቦታ የያዙ ተወላጆች ነበሩት፡፡ ኤርትራና የትግራይ ተወላጆች በአንድነት ተደምረው 11.1 በመቶ የጄኔራልነት ቦታ ሲይዙ ጉራጌዎች 4.4 ከመቶ የጄነራልነት የሥልጣን ማእረጉን ይዘው እንደነበር ጥናቱ ያሳያል፡፡ በደርግ ዘመን የከፍተኛ ወታደራዊ ሥልጣን ብሄራዊ ስብጥር ከአጼ ኃይለሥላሴ ዘመን በከፍተኛ ደረጃ የተሻሻለ መሆን ብቻ ሳይሆን በንጉሱ ዘመን ያልታዩ ተጨማሪ የብሄረሰቦችን ስብጥር ለማካተት መብቃቱን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በንጉሡም ሆነ በደርግ ጊዜ ወታደራዊ ሙያና ታማኝነት እንጂ ዘር የዛሬን ያህል ጉልህ የሆነ ሚና የነበረው ጉዳይ እንዳልነበረ ጥናቱ በግልጽ ያሳያል። በዚህም ምክንያት በደርግ ጊዜ ኢትዮጵያ የወላይታና የሃረሪ ተወላጆች የሆኑ ጄነራሎችን ለማየት በቅታ ነበር፡፡ ዛሬ በዘመነ ወያኔ ይኸ ቀርቶ በሕዝብ ብዛት ትላልቅ ከሆኑትም ከኦሮሞና ከአማራው ብሄረሰቦች የመጡ ወታደራዊ ጄኔራሎች ማግኘት አይቻልም፡፡

ስለ አጼ ኃይለሥላሴና ስለደርግ ዘመን የከፍተኛ መኮንኖች የብሄር ስብጥር ስናወሳ መረሳት የሌለበት ነገር አለ። በእነዚህ ሥርዓቶች የጦር መኮንኖቹ ማእረግ የተሰጣቸው ባገኙት ስልጠና እና ትምህርት እንዲሁም በተግባር ባሳዩት ብቃት እንጂ ዛሬ ወያኔ እንደሚያደርገው ዘርን መለኪያ በማድረግ አልነበረም፡፡ ብዙዎቹም ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የሚያገለግሉት ሥርዓት በሃገርና በወገን ላይ የሚያደርሰው ግፍ ከፍቷል ብለው ባመኑበት ሰዓት ለራሳቸው ሕይወት ሳይሳሱ ሁኔታዎች እንዲቀየሩ ሥልጣን በሰጧቸው ገዥዎቻቸው ላይ እያመፁ የሕይወት መስዋትነት የከፈሉ ናቸው። መለስ ዜናዊ ከራሱ ጠባብ ቡድን ብቻ የሰበሰባቸው ጭፍን ሎሌ ጄኔራሎችን ከቀድሞዎቹ የሃገሪቱ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ጋር ማነጻጸር ፈጽሞ አይቻልም።

የወያኔን ዘረኝነት አስከፊ የሚያደርገው ሌላው አቢይ ጉዳይ ያለበንት ዘመን ነው። ዛሬ የመሳፍንትና የነገሥታት ወይም የወታደራዊ አምባገነኖች ዘመን አይደለም፡፡ ዛሬ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ይህ ዘመን እኩልነት፣ ነጻነትና ዴሞክራሲ የአንድ ሃገር የፖለቲካ ሥርዓት መመዘኛ መስፈርቶች መሆናቸው ሰፊ ተቀባይነት ያገኘበት ዘመን ነው፡፡ በዚህ ዘመን የጦር ሠራዊትን በዘር መሥፈርት መገንባት ከባድ ወንጀል ነው።

በመጨረሻም የግንቦት 7 ምርምር ቡድን ይህን ጥናት ሲያደርግ ፍትሃዊ የጦር ሠራዊት አደረጃጀት የሕዝቡን ስብጥር መሳ ለመሳ መወከል አለበት ማለቱ አይደለም። ግንቦት 7 ሙያዊ ብቃትና ሕዝባዊ ታማኝነት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሹመት መሥፈርት መሆን አለባቸው ብሎ ያምናል። በተጨማሪም ሙያዊ ብቃትና ሕዝባዊ ታማኝነት ከብሄር/ብሄረሰብ ወይም ዘር ጋር እንዳይያያዙ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል እኩል የትምህትና ስልጠና እድል እንዲያገኝ፤ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል እኩል የሃገሩ ባለቤት እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል ብሎ ያምናል።

በዚህ ፋንታ ከአንድ አካባቢ የተውጣጡ ዘረኞች የአገሪቱን ዋነኛ የመንግሥት መዋቅር አንቀው ይዘው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ሲያዋርዱ መናደድ አይበቃም። የሥርዓቱን እድሜ ለማሳጠር ከምንጊዜውም በላይ ተግቶ መሥራት ይገባል እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## መለስ ዜናዊ ተቃዋሚዎቹን እንክርዳዶች፣ . . . ከገጽ 1 የዞረ

የመለስ ዜናዊን ንግግር ተከትሎም የተለያዩ አስተያየቶችም እየተሰነዘሩ ነው። አንዳንዶች መለስ ዜናዊ በትግራይ ውስጥ እያየለ የመጣው ተቃውሞ እንቅልፍ እንደነሳው የሚያሳይ ነው ያሉ ሲሆን፣ ለዚህ አባባለቸው ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድም "የትግራይ ህዝብ አመጽ እንዳታነሳ በራሴና በማእከላዊ ኮሚቴ ስም እማጸንሀለሁ" ያለውን ለአብነት ጠቅሰዋል።

ሌሎች ወገኖች ደግሞ ሰውየው ይህን የሚያደርገው በቅንጅት አመራሮች ላይ እንደፈበረከው አይነት ክስ በመፈብረክ ተቃዋሚዎችን ለማሰር ከአሁኑ የክስ ቻርጅ እያዘጋጀ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

እነዚህ አስተያየት ሰጪዎች እንደሚሉት መለስ ዜናዊ በዚህ ንግግሩ ስልጣን በምርጫ ፈጽሞ እንደማይለቅ ያሳወቀ ሲሆን፣ እንዲያውም ለምርጫ የሚወዳደሩት እንደጠላት መፈረጅና መወገዝ እንዳለባቸው ፣ የትግራይም ህዝብ ጠላት በመሆናቸውም መቀጣት እንዳለባቸው ያለ ሀፍረት በግልጽ ተናግሯል ብለዋል። እነዚህ አስተያየት ሰጪዎች አክለውም፣ "ሰውየው በግልጽ ይህን እየተናገረ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ይኖራል ብለው የሚያስቡ ተቃዋሚዎች የመለስ ዜናዊን ማንነት ለመረዳት የተሳናቸው የሁዋዎች ናቸው" ሲሉ ይናገራሉ።

## የወያኔው አገዛዝ የመጀመሪያ ደረጃ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ኢትዮጵያ ይህን የሚለኒየም ግብ እውን እንደምታደርገው መግለጹ በርካቶችን ከማስገረም አልፎ እንዲህ አይነት ባየር ላይና ምንም በማይጨበጥ መልኩ መለስ ለምን እንደዚህ አይነት ማረጋገጫዎችን እንደሚሰጥ ሊረዱ አለመቻላቸውንም እነኚሁ ታዛቢዎች አክለው ገልጸዋል። ታዛቢዎቹ እንደገለጹት መለስ ካሁን በፊትም ቢሆን ባደባባይ ምንም የተራበ ኢትዮጵያዊ የለንም፤ ርዳታችሁን ብታቆሙ ያንድም ሰው ህይወት አያልፍምና ሌሎችንም መጨበጫ የሌላቸው ውሸቶች መዋሸት የጀመረው ዛሬ እንዳልሆነና ያሁኑም ድርጊቱ ከዚህ የተለየ እንዳልሆነ እምነታቸዉን ገልጸዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዜና በሱዳን አዋሳኝ ያለው የኢትዮጵያ ድንበር ለሱዳን ተቆርሶ እንዲሰጥ በአማራው ህዝብ ላይ ፈርዶ የፈረመዉና ለዚህም ዉለታው በወያኔው አገዛዝ የትምህርት ሚኒስቴር ሚንስትርነትን ስልጣን የተረከበው ደመቀ መኮነን አለቃው ያሰማውን ዲስኩር እንደገደል ማሚቶ በማስተጋባት ኢትዮጵያ በትምህርቱ መስክ ከፍተኛ ድል ያስመዘገበች መሆኑንና ለዚህም ድል ዋነኛው ተጠቃሽ መንግስት ያሳየው ቁርጠኝነት ነው በማለት በስብሰባው ላይ የተናገረ መሆኑን ለማወቅ ቺለናል።



የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 93 የካቲት 18 2002 ዓ.ም፤ ገጽ.3

# ምርጫ ለምንና ለማን?

ከኤሉና ገብረማርያም

የምርጫ 2002 ዓም ዝግጅት ተጀምሯል። ህወሀት /ኢህአዴግ መራጮች የምርጫ ካርድ እንዲወስዱ እየወተወተ ነው። የተቃዋሚ ፓርቲዎችም እጩዎቻቸውን አቅርቡ ተብለው በማቅረብ ላይ ናቸው። አሁን እንደሚታየው አብዛኛው የተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫው ለመሳተፍ ዝግጅት እያደረጉ ነው። ተቃዋሚዎች የምርጫ ዝግጅት ያድርጉ እንጂ ምርጫውን እናሸንፋለን ብለው በድፍረት ሲናገሩ አይሰማም። ውስጣቸው ምርጫው የተበላ እቁብ መሆኑን አምኖ የተቀበለ ይመስላል። ለነገሩ ወያኔ ከምርጫ 97 በሁዋላ ስልጣን ከእጁ እንዳይወጣ ለማድረግ የወሰዳቸውን እርምጃዎች የተከታተለ ሰው ምርጫው የተበላ እቁብ መሆኑ አይጠፋውም ። ከግንቦት 97 ምርጫ ማግስት ወያኔ ሰልጣኑን በምርጫ ወይም በጡጫ ለማቆየት የተለያዩ ስራዎችን ሰርቷል። የጸረ ሽብረተኝነት ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚቆጣጠረው ና የሚዲያ ህግጋት ለዚሁ አላማ ተብለው የተዘጋጁ ናቸው። እንዲሁም ኢትዮጵያውያን በምግብ፣ በገንዘብ፣ በስራ ቅጥር ፣ በእድገትና በማስፈራራት የወያኔ / ኢህአዴግ አባላት እንዲሆኑ አድርጓል። ከግንቦት 97 በሁዋላ ባደረገው እንቅስቃሴ ወያኔ አራት ሚሊዮን አባላትን ለማፍራት መቻሉን በኩራት ይናገራል። በርግጥ ወያኔ በአለፉት አምስት አመታት አባላትን ለማፍራት ከተጠቀመበት ዘዴ አንጻር ሲታይ አራት ሚሊዮን በጣም ትንሽ ቁጥር ነው። ቁጥሩን ከኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር አንጻር አወዳድረን እንመልከተው፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር 82 ሚሊዮን ነው ። የትግራይ ህዝብ ደግሞ 6 ሚሊዮን ነው። ከ6 ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ 2 ሚሊዮን የሚሆነው የትግራይ ህዝብ ወያኔን ይደግፈዋል ብንል፣ ቀሪው 2 ሚሊዮን የሚሆነው ደጋፊ ያለው በሌሎች ክልሎች የሚኖር ነው ማለት ነው። ይህ ማለት ቀሪው የወያኔ 2 ሚሊዮን ደጋፊ የሚኖረው 74 ሚሊዮን የሚሆነውን ቁጥር በሚሸፍነው በሌሎች ክልል ህዝቦች ነው ማለት ነው። 2 ሚሊዮን የሚሆነውን ደጋፊ ከ74 ሚሊዮን ከሚሆነው የሌሎች ክልል ህዝቦች አንጻር በመቶኛ እናስላው ብንል ፣ በሌሎች ክልሎች ያለው የወያኔ ደጋፊ ከ 2 በመቶ አይበልጥም። የትግራይ ድጋፉን ስንመለከት ግን ከ 40 በመቶ በላይ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህንን ቁጥር ወስደን በክልሎች ውሰጥ ባለው የህዝብ ብዛት ብንተነትነው የወያኔ ደጋፊ ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው። በስሌቱ መሰረት ለምሳሌ በአማራ ክልል ያለው ደጋፊ ከ60 ሺ አይበልጥም፣ ይህ ማለት የአንድን ወረዳ ህዝብ ቁጥር እንኳ የሚወክል አይደለም። ከዚህ ስሌት እንደምንረዳው ወያኔ ኢትዮጵያውያንን እያስገደደ አባላቱ ለማድረግ ቢሞክርም ፣ ከትግራይ ውጭ ያገኘው ደጋፊ ቁጥር እጅግ አነስተኛ መሆኑን ነው። ምናልባት የወያኔ ደጋፊዎች ቁጥር ብዙ መስሎ የሚታየው ከተቃዋሚዎች አባላት ቁጥር ጋር ስለሚነጻጸር ነው። ምርጫው በትክክል ቢካሄድ ኖሮ፣ ወያኔ አሁን ባለው የአባላት ቁጥር መሰረት ከ32 ሚሊዮን መራጭ ውስጥ ሊያገኝ የሚችለው ድምጽ ከ10 በመቶ አይበልጥም ማለት ነው። በአጭሩ የውዴታ ግዴታ ደጋፊዎቹን ተጠቅሞ ምርጫውን ሊያሸንፍ አይችልም ማለት ነው። ወያኔ ይህን ጠንቅቆ ሲለሚያውቅም ምርጫውን አበላሽተው አሸናፊነቱን ሊያረጋግጡለት የሚችሉትን ሌሎች ዘዴዎች መጠቀም አለበት። ከእነዚህ ዘዴዎች መካከል አንዱ የ ምርጫ ቦርድ የሚባለውን ተቋም በራሱ ታማኞች እንዲያዝ ማድረግ ነው። ይህንንም አድርጓል። ምርጫ ቦርድን እስከዛሬ የሚመራው ተስፋየ የተባለ የወያኔ ታማኝ ሰው ነው። ወያኔ ይህ ሰው ፈጽሞ እንዲለወጥበት አይፈልግም። ሰውየውን በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች በመያዝ ወያኔ ያለውን ነገር ብቻ እንዲተገብር እያደረገው ነው። አንዳንድ ጊዜ ነገሮች ገፍተው ከምርጫ ቦርድ አቅም በላይ ሲሆኑ በአምሳሉ የተፈጠሩትን የፖሊስና የመከላከያ ሀይሎች ከዚያም እልፍ ሲል ዳኞችን አሰማርቶ ጨዋታውን ያሸንፋል። ወያኔ እነዚህን ሁሉ እርምጃዎች ከወሰደ በሁዋላ ነው የምርጫ እቃ እቃ ጨዋታ እንጫወት የሚለው። ተቃዋሚዎችም በየዋህነት ወይም አማራጭ በማጣት ነው በዚህ የምርጫ ጨዋታ ውስጥ ገብተው ለመደነስ የተሰለፉት። ምርጫው የተበላ እቁብ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው።

ለነገሩ ምርጫው ፍትሀዊና ትክክለኛ ይሆናል ቢባል እንኳን በዚህ ምርጫ ውስጥ ለመሳተፍ የማያስችሉ በርካታ ምክንያቶች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ወያኔ በመፈንቅለ ህዝብ ስልጣን የያዘ ህገወጥ ሀይል ነው። በምርጫ 97 ወቅት ህዝቡ ህዝበ- ውሳኔ አድርጎ ወያኔን "በቃህኝ" ብሎታል። ህዝቡ "በቃህኝ" ቢልም ወያኔ ግን ህዝቡን "አልበቃህኝም" ብሎ ስልጣኑን ቀምቶ እየገዛው ነው። በዚህም የተነሳ በህዝቡና በወያኔ መካከል ያለው ፍጥጫ እስከዛሬ እንደቀጠለ ነው። ህዝቡ በተደጋጋሚ ጊዜያት ወያኔን ስልጣኔን መልስልኝ እያለው ነው። ታዲያ በዚህ ምርጫ ወያኔን ለማጀብ መሳተፍ ፣ ህዝቡን "ተሳስተሀል" እንደማለት ይቆጠራል። ከወያኔ ጎን አብሮ መዋልም ህዝብን ከጀርባ ሆኖ አብሮ እንደመውጋት ይቆጠራል። ህዝቡ ስልጣኔ ይመለስልኝ ሲል፣ ስልጣን የለህም ማለትን ያስከትላል። ይህ ደግሞ ህዝብን መናቅ ይሆናል። የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን ምርጫ እንደምርጫ ያልቆጠረው በሌላ በምንም ምክንያት ሳይሆን "በ97 ቱ ምርጫ የተቀማሁት ስልጣኔ ይመለስልኝ፣ ካልተመለሰልኝ ግን በዚህ ምርጫ አልሳተፍም" የሚል አቋም በመውሰዱ ነው። ታዲያ ከወያኔ ጋር አብሮ በምርጫ ውስጥ መግባት ህዝቡን "ያነሳሀው የስልጣን ጥያቄ ትክልል አይደለም" ወደ ሚል ድምዳሜ ያደርሳል። በአጭር አነጋገር በዚህ ምርጫ መሳተፍ የወያኔን መፈንቅለ ህዝብ ማጽደቅ ነው። ህገወጡን ወያኔ ህጋዊ ማድረግ ነው። ይህ ደግሞ ከወንጀለኛ ጋር የተባበረ ወንጀለኛ ነው የሚለውን ህግ ያስጠቅሳል።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በዚህ ምርጫ መሳተፍ ማለት ለዲሞክራሲ ሲሉ የተሰዉትን የግንቦት ሰማእታት በድጋሜ እንዲሰው ማድረግ ማለት ነው። ወያኔ በምርጫ 97 ከ200 በላይ ወጣቶችን ገድሎአል። በሺዎች የሚቆጠሩትን አቁስሎአል። በርካቶችንም አስሮአል፣ ንብረታቸውን ዘርፏል፣ ከቀያቸው አፈናቅሎአል። ይህ ሁሉ ወንጀል ነው። ወያኔንም በወንጀል የሚያስጠይቀው ነው። እነዚህ ሁሉ የግንቦት ሰማእታት ወያኔን ለመፋረድ ይፈልጋሉ። ደማቸው መስዋትነታቸው በከንቱ እንዲቀር አይፈልጉም። ታዲያ በዚህ ምርጫ ወንጀለኛ የሆነውን ቡድን አጅቦ መሳተፍ፣ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የተሰውትን ሰማእታት ደም ደመ ከልብ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን፣ ለወያኔ ጥይት አድናቆትንና ከበሬታን እንደመስጠት ይቆጠራል። ገዳዩን ትክክልነው የሰራሀው ፣ ወንጀለኛም አይደለህም እንደማለት ይወሰዳል። በሌላ አነጋገር ወያኔን ከተጠያቂነት አዳንነው ማለት ነው። እንኳን የሰው ነፍስ የውሻ ነፍስ ከፍተኛ ከበሬታ ባገኘበት ጊዜ፣ ከ200 በላይ የሚሆኑ ወጣቶችን ደም በየጎዳናው ከረጨው ሀይል ጋር መተባበርና የእርሱ አጃቢ ሆኖ መገኘት ፣ ለዲሞክራሲ ሲሉ ደማቸውን ባፈሰሱት ወጣቶች ደም ፊትን እንደመታጠብ ይቆጠራል። የሰማእታቱ የነብዩና የሌሎችም ህጻናትና ወጣቶች ደም ከሰማይ ቤት ይጣራል። ደማችን በየጎዳናው የተረጨው ለዚህ ነበር ወይ ይላል። በዚህ ምርጫ መሳተፍ ማለት እንግዲህ በእነነብዩ ደም መታጠብ ማለት ነው። የእነነብዩን ደም ያፈሰሰውን ነፍሰገዳይ አበጀህ ማለት ነው።

በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ በዚህ ምርጫ መሳተፍ ማለት ዘረኝነት እንዲስፋፋ፣ የአገር ህልውና እንዲጠፋ መተባባር ማለት ነው። ወያኔ ዘረኛ ነው። መለስ ዜናዊ ከትግራይ ህዝብ ከዚያም ካወረደ ከአድዋ ህዝብ ውጭ ያለው ህዝብ ቢጠፋ ግዱ አይደለም። እርሱ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ህዝብ ከህዝብ ቢተላለቅ በስልጣኑ ላይ ተጽኖ እስካላመጣ ድረስ ደንታው አይደለም። የትግራይን ህዝብ ወርቅ የሌላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ጠጠር አድረጎ የሚመለከት ዘረኛ አገዛዝ ነው። እንዲሁም ለአገር ሉአላዊነት የማይቆረቆር የከሀዲዎች ስብስብ ነው፣ የመለስና የበረከት ቡድን። ለስልጣን እድሜው ማራዘሚያ ሲል፣ አባቶቻችን በደምና ባጥንታቸው ያስከበሩትን ዳር ድምበር እንደ አምባሻ እየቆረሰ ለጎረቤት አገሮች ሲሰጥ ትንሽ የማይሰቀጥጠው፣ የአገሪቱ ህዝብ ተርቦ መሬት እየከፋፈለ ለቻይና፣ ለአረብና ለህንድ ነጋዴዎች ሲያከፋፍል፣ ለዘመናት የቆየውን የአባይን ውሀ ባለቤትነት ለግብጽ አሳልፎ ለመስጠት ሲደራደር እንዲሁም ለገንዘብ ብሎ ህጻናትን በውጭ አገራት ሲቸበችብ ትንሽም ቢሆን የማይሰቀጥጠው ወራዳ የሽፍታ ጥርቅም ነው የመለስና የበረከት ስብስብ። በዚህ ምርጫ መሳተፍ ማለት ታዲያ ይህ አጥፊ ቡድን በስልጣን ላይ እንዲቆይ እንደገና መፍቀድ ማለት ነው። በምርጫ ስም እያመካኘ አገር እንዲያወድም መተባበር ማለት ነው። ህዝብ በዘረኝነት መርዝ ተበክሎ እንዲጫረስ፣ በረሀብና በእርዛት እንዲያልቅ መተባበር ማለት ነው። ይህ ደግሞ በአገር ክህደት ወንጀል ያስጠይቃል።

በቅርቡ እንግሊዝና ሆላንድ በኢራቅ ላይ የተደረገውን ወረራ አስመልክቶ መንግስቶቻቸው የወሰዱዋቸውን አቋሞች በመመርመር ላይ ናቸው። አብዛኞቹ እንግሊዛውያን ከአሜሪካ ጎን ቆሞ የኢራቅን ወረራ የመራው ጠቅላይ ሚኒስትር ቶኒ ብሌየር ለፍርድ እንዲቀረብ እንደሚፈልጉ ገልጸዋል። በሆላንድ ደግሞ የባልኬኔዲ ካቢኔ ያለበቂ የፓርላማና የህግ ድጋፍ ለወረራው ፖለቲካዊ ድጋፍ ስለሰጠ ህዝቡን በይፉ ይቅርታ ጠይቆ ፣ የአገሪቱን መንግስት ከመበታተን አድኖአል። ይህ ሁሉ ምርመራ ያስፈለገው ለምንድነው? መልሱ ግልጽ ነው። እንዲህ አይነት ህገወጥ ስራዎች በድጋሜ እንዳይከሰቱ ለሌሎች ተተኪ መሪዎች ትምህርት ለመስጠት ነው። በእኛ ሁኔታ ግን በምርጫ ስንሳተፍ ለወያኔ የምንሰጠው ትምህርት ይህ አይደለም፤ ቀጥል በርታ እያልነው ነው። ከጥፋቱ እንዲማር፣ ተምሮም እንዲታረም ሳይሆን፣ ካጥፊነት ወደ አውዳሚነት እንዲሸጋገር እያደረግነው ነው። ቀደም ብሎ በአርባጉጉ፣ በጋምቤላ፣ በሲዳማ፣ በኦሮሚያ፣ በጎንደር ወዘተ ተመሳሳይ ግድያዎች ሲፈጽም እንዳላየን ሆነን ስላለፍነው፣ በጠራራ ጸሀይ 200 ወጣቶችን አርዶ ደማቸውን በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ አፈሰሰው፤ በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየገባ ህጻናትን በጥይት ፈጃቸው። በኦጋዴን እናቶችንና ሴቶችን ከዛፍ ላይ ሰቀላቸው። በሶማሊያ በሰላማዊ ዜጎች ላይ መድፎችን ተኩሶ ጨረሳቸው። ይህ ሁሉ የሆነው ገና ከድሮ (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

## ወያኔ የስኳር እጥረት ሆን ብሎ እንዲባባስ በማድረግ ትርፍ እያጋበሰ እንደሚገኝ ነዋሪዎች አስታወቁ

በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የስኳር እጥረት እየታየ መሆኑን አዲስ አበባ የሚገኘው ዘጋቢያችን መርካቶ ዉስጥ በመዘዋወር ያነጋገራቸው ኗሪዎችና የስኳር ነጋዴዎች የገለጹ ሲሆን፣ በዚህም የስኳር እጥረት እጅግ በርካታ የሆነውና በድህነት አለንጋ እየተገረፈ ያለው ህብረተሰብ ከእለት የምግብ ሰንጠረዡ ዉስጥ ስኳርን እንዲያስወጣ እየተገደደ መሆኑ ታውቋል።

የወያኔው አገዛዝ በተለያየ መልክና ዘዴ የሃገሪቱን ሃብት ሙሉ በሙሉ እየተቆጣጠረ መሆኑ እየተገለጸ ባለበት ባሁኑ ወቅት በሃገሪቱ በታየው የስኳር እጥረት እምብዛም እንዳልተገረሙ የገለጹት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ለዚህም ችግር ዋና ምክንያቱ ይሄው አገዛዝ አይኑን ጨፍኖ በጭካኔ የሃገሪቱን ንብረት ጨርሶ ለመሙዋጠጥ የሚያደርገው ሩጫ አካል ነው ብለዋል።

ዘጋቢያችን የውስጥ አዋቂ ምንጮችን ጠቅሶ በላከልን ዘገባ እንደገለጸው የወያኔው አገዛዝ አነስተኛና መከከለኛ የሆኑ ነጋዴዎችን ሙሉ በሙሉ ከገበያ በማስወጣትና በራሱ ኩባንያዎችና ቸርቻሪዎች በማስያዝ የንግዱን ዘርፍ የተቆጣጠረው ከረጂም ጊዚያት በፊት መሆኑን በመግለጽ ፤ አሁንም ለዚህ የስኳር እጥረት መከሰት ምክንያቱ ወያኔ በሃገሪቱ ያለውን የስኳር ምርት በማግበስበስና ወደማከማቻ መጋዝኖች በማስገባቱ አሁን በገበያ ላይ ያለው ከፍተኛ የስኳር እጥረት እንዲከሰት አድርጓል ብሏል። ወያኔ ይህን በገበያ ላይ የነበረ ስኳር አግበስብሶና እጥረቱም እንዲከሰት ካደረገ በኋላ የተወሰነውን ያለምንም ተቆጣጣሪ በፈለገውና ከፍተኛ በሆነ ዋጋ እንደሚቸረችረው የተወሰነውን ደግሞ የግል ካዝናዉን እንዲሞሉለት በእጂ አዙር ለተቆጣጠራቸው ለጂናድና ኢትፍሩት ለተባሉት ድርጅቶች እንደሚያስረክባቸው ታውቋል።

ወያኔ በሞኖፖል አፍኖ በያዘው የብዙሃን መገናኛ አማካኝነት ለተፈጠረው የስኳር እጥረት ሌሎችን በዝቅተኛና በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ነጋዴዎችን ደብቀዋል በማለት ጂራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል አይነት ውንጀላ እየፈጸመ መሆኑን ለማወቅ ተቿሏል።

በተያያዘ ዜናም በኢትዮጵያ የሚታየው የአኮኖሚ ቀውስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መሆኑን ምንጮች ይናገራሉ። በውጭ እርዳታ ሲገነቡ የነበሩ ፕሮጀክቶች የወያኔ ባለስልጣናት አብዛኛውን ገንዘብ እየዘረፉ በውጭ አገር ባንኮች በማስቀመጣቸው እንደተጀመሩ ቀርተዋል። በርካታ ባንኮችም ለወያኔ ኩባንያዎች በማበደራቸውን ኩባንያዎችም ገንዘቡን ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የግል ባንኮችና የመንግስት ባንኮች አይተውት በማያውቁ የገንዘብ ችግር ውስጥ መግባታቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

### የመከላከያ ሰራዊት አባላት መሳሪያቸውን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተያያዘ ዜና ወያኔ የወያኔን የዘረኝነት ፖሊሲ በመቃወማቸው ብቻ የሀሰት ፍርድ የተፈረደባቸው እነ ብ/ጄ ተፈራ ማሞና አራት ባልደረቦቻቸው በሞት እንዲቀጡ አቃቢ ህግ ይግባኝ መጠየቁን ያገኘነው መረጃ አመልክቷል። በቀለኛው ወያኔ የእድሜ ልክ እስራት ማስፈረዱ ስላላረካው በሞት እንዲቀጡለት የተለመደውን ድራማ ለመስራት ሸር ጉድ እያለ መሆኑን ያገኘነው መረጃ አመልክቷል። የይስሙላ ይግባኝ የተጠየቀባቸው የነጻነት ታጋዮች ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ ብ/ጄ አሳምነው ጽጌ፣ ኮ/ል ደምሰው አንተነህ፣ ሻለቃ መኮንን ወርቁ እና ኮ/ል አለሁበል አማረ በሌሉበት ነው። የወያኔ አስቂኝ ድርጊት አገዛዙ ምን ያክል ውጥረትና ፍርሀት ውስጥ እንደገባ ያሳያል የሚሉ በርካቶች ናቸው።

### ወያኔ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘጋቢያችን ሪፖርት ያደረጉለትን አባል ተማሪዎች ድርጊቱን አስመልክቶ አስተያየታቸው ምን እንደሆነ ላቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ "እኛ ራሳችን ለወያኔው አገዛዝ የይስሙላ ድጋፍ እንድንሰጥ የተገደድንበት ዋናው ምክኒያት ከችግረኛ ቤተሰብ የወጣን በመሆናቺንና ትምህርታቺንን ስናጠናቅቅ በስራ ማጣት እንዳንንገላታ በመፍራት እያደረግነው ያለነው ተግባር ነው እንጂ በፍጹም ልባቺንን ለወያኔ ክፍት አድርገን ወንድምና እህቶቻችንን አሳልፈን መስጠቱ የሚታሰብ ጉዳይ አይደለም" ካሉ በኋላ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በ1997 ምርጫ ወቅት እንኳን የሌላ ክልል የወያኔ አባላት ይቅርና የትግራይ ተወላጅ የሆኑት ደጋፊዎቹ እንኩዋን በነጻነት ድምጽ በሰጡባት ነጻ ሳጥን አንዳቸውም ወያኔን እንዳልመረጡ በማስታወስ ባሁኑም ምርጫ ተመሳሳይ ሁኔታ እስከተፈጠረ ድረስ ለወያኔ ሊደረግ የሚችል ምንም የተለየ ድጋፍ ሊኖር እንደማይቿል ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ወያኔ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የሚደረግ ለማስመሰል የማያደርገው ጥረት እንደሌለ ታውቋል። ህዝቡ ለምርጫ ያለው ፍላጎት ፈጽሞ በተመናመነበት ሰአት፣ ወያኔ የውጭ አገር ጧሪዎቹን ለማስደሰት አንዳንድ መለስተኛ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ነው፡፤ የአገኘነው መረጃ እንደሚአመለከተው ወያኔ የአንዳንድ ተቃዋሚ አባላትን መሪዎች ከእስር የፈታ ቢሆንም፣ ህዝባዊ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ ብሎ የፈራቸውን እንደነ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያሉትን የነጻነት አርበኞች ለመፍታት ግን ፈቃደኛ ሊሆን አልቻለም። ወያኔ ራሱ እንደሚአሸንፍ ባረጋገጠበት ምርጫ በሂደቱ የፈራ አስመስሎ ራሱን በማቅረብ ምርጫው የተሟማቀ ምርጫ እንዲመስልለት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው።

## ሃይለ ሀሳብ

. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

አንተባበርህም ስላላልነው። አሁንም ቢሆን በስልጣን ላይ እንዲቆይ የህጋዊነት ሽፋን ስናሰጠው፣ እስከዛሬ ከሰራው ግፍም በላይ ሌሎችን ግፎች እንዲሰራ መተባበራችን ነው።

በመጨረሻ በዚህ ምርጫ መተባበር ማለት የአለማቀፍ መንግስታት ለወያኔ የሚሰጡትን ድጋፍ እንዲጨምሩና ዘላለም ወያኔን እየደገፉ እንዲኖሩ ማድረግ ነው። እንደሚታወቀው የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን፣ የግንቦት 97 ምርጫ አለማቀፍ መስፈርቶችን እንደማያሟላ ገልጾ ነበር። የድጋሜ ምርጫ እንዲካሄድም ጠይቆ ነበር። የአለማቀፉ ማህበረሰብም ምርጫውን ተከትሎ ለተገደሉት ወጣቶች ፣ ወያኔ ሀላፊነቱን እንደወስድ በመወትወት ላይ ነበር። በምርጫ መሳተፍ ማለት የአውሮፓ ህብረትም ሆነ የአለማቀፉ ማህበረሰብ በወያኔ ላይ የያዙትን አቋም እንዲቀይሩ መገፋፋት ነው። በተቃዋሚዎች ላይ ያላቸውን ተስፋም እንዲቆርጡ የሚያደርግና ወያኔን ለዘለአለም እሸሩሩ ብለው እንዲaይዙ የሚያደርግ ነው።

ታዲያ በምርጫ መሳተፍ ይህ ሁሉ ጉዳት ካለው ምን ማድረግ ይሻላል? መልሱ በጣም ቀላል ነው- በምርጫው አለመሳተፍ ። ህዝቡ አሁን እየወሰደ ባለው እርምጃ ገፍቶበት ካልተመዘገበ፣ በግድ ተመዝግቦም ከሆነ የምርጫ ወረቀቱን በምርጫው እለት ካበላሸው ወይም ጠፋብኝ ብሎ ካለ ወይም ሰበብ አስባብ አፈላልጎ ወደ ምርጫ ጣቢያው ከመሄድ ከታቀበ፣ ወይም በድምጽ መስጫ ቀን የምርጫው ካርድ ዋጋ እንዲያጣ ለማድረግ በተከለከሉ ቦታዎች ላይ አሳሳች ምልልክቶችን ካደረገ ለወያኔ ምርጫ ተባባሪ አልሆነም ማለት ነው። ተቃዋሚዎችም ደጋፊዎቻቸውን ይህን እንዲያደርጉ በሚስጢር መንገር አለባቸው።የተቃዋሚ መሪዎች ይህን ማድረግ ያለባቸው ራሳቸውን ከምርጫ ማግለል ካልቻሉ ነው። ራሳቸውን ከምርጫ ማግለል ከቻሉ ግን እሰየው ነው። የህን እንዲያደርጉም እመክራለሁ። ይህን ካደረጉም ህዝባዊ ድጋፋቸው ይጨምራል፣ ህዝባቸውንም ለፍልሚያ በደምብ ማዘጋጀት ይችላሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን ተፋልሞ ለመሞት አሁንም ዝግጁ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ የማይፈልገው ወያኔንና ሊያጅቡት አብረው የተነሱት ሀይሎች ነው።

### ኤርትራዊያን በአገራቸው ላይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አቶ ናእምን "በሰልፉ ላይ እንዴት ኢትዮጵያዊያን ሊገኙ ቻሉ?" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በሰልፉ ላይ መገኘት ብቻ ሳይሆን ሰልፉ ከፍተኛ የሆነ ድጋፍን እንዲያገኝ በሰሜን አሜሪካ እንዲሁም ባውሮፓ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በድረገጾችና በሬዲዮኖች የማስተዋወቅ ጥረት ማድረጋቸውን ጠቁመው "አሁን ባለንበት ዓለም ሁሉም ነገር የተያያዘ ሲሆን ይህም ሰልፍ በተለይ ኢትዮጵያዊያንን ከሚመለከትባቸው መሰረታዊ ምክኒያቶች ውስጥ አንደኛው እገዳው በጣም ኢ-ፍትሃዊ በመሆኑ ነው ካሉ በኋላ ሌላው ደግሞ በኤርትራም ሆነ ባካባቢው ላለው ችግር፣ ቅራኔና ፍጥጫ በአንደኛ ደረጃና በዋነኛነት ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው የወያኔው አምባገነናዊ ዘረኛ መንግስት መሆኑን የማሳወቅ መልእክት ለማስተላለፍ ነው" ብለዋል። ቀጥለውም "ይህ የተባበሩት መንግስታት ድርጂት የወሰደው ውሳኔ ፍጹም ፍትሃዊ ያልሆነ ለመሆኑ ማስረጃችን ባንድ በኩል ኤርትራ ላይ እቀባ ሲያደርግ ነገር ግን በዘር ማጥፋትና በጦር ወንጀሎች ተጠያቂ የሆነውንና በሶማሌ ውስጥ ላለው ሁኔታ እዚህ ደረጃ መድረስ እንዲሁም ለእስልምና አክራሪነት መስፋፋት ዋና ተጠያቂ የሆነው ወያኔ ከተባበሩት መንግስታትም ሆነ እዚያ ውስጥ ካሉት ሃያላን ሃገራትና ተባባሪዎች አንድም ቀን እንኳን እገዳ ቀርቶ ምንም አይነት ተቃውሞ ሲያሰሙት ባለመታየታቸው እንደሆነ ገልጸው የተወሰደውም ውሳኔ ከዚህ አንጻር ያለውን ኢፍትሃዊነት ለማሳየት ነው" ብለዋል።

በመጨረሻም "ይህ ሰልፍ እዚያ አካባቢ ሁለንተናዊ ሰላም ተፈጥሮ በሰላምና በጋራ ለምንኖርበትን ሁኔታ የመጀመሪያው ደረጃ ፈር ቀዳጂ ይሆናል ከሚልም ሰፋና ረዘም ካለ ራዕይና የፖለቲካ እይታ በመነሳት በጋራ መካሄዱንና ኢትዮጵያዊያንም ከኤርትራዊያን ጋር ለመቆም የወሰንነው አንድነታችንን ለማሳየት ነው" ካሉ በኋላ "ወደፊት የኢትዮጵያ ህዝብ የመረጠው ኢትዮጵያዊና ዲሞክራሲያዊ ስርአት በኢትዮጵያ ውስጥ ሲመጣ ከኤርትራ ህዝብና ከኤርትራ መንግስት ጋራ ሁሉንም ነገር በሰላም ለማድረግና የሁለቱን ሃገሮችና ያካባቢውን ሰላም ለማስፈን እንዲሁም መልካም አስተዳደርን፣ የሃገራዊ ብቻ ሳይሆን የግለሰብ ነጻነትን ጭምር ለማምጣት መሰረት ያደረገ ረጂም ግንኙነት ይኖረናል፤ ሊኖረንም ይገባል ብለን እናምናለን ለዚህም ደግሞ ከወዲሁ ህዝብ ለህዝብ ተገናኝተን በጋራ መስራት አለብን በማለት በሰልፉ ላይ መለእክታችንን አስተላልፈናል" ብለዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661